# ዘመነ አዲስ ኪዳን

## የፍልስጥኤም (የፓሌስቲን) ጂኦግራፊ

## ክፍለ ሐገሮች

## (አንደኛውን ካርታ ተመልከት)

፩፤ <u>ይሁዳ</u> ከፍልስጥኤም አውራጃዎች ሁሉ በስፋት አንደኛና አስቀድሞም ለይሁዳ፣ለብንያም፣ለዳንና ለስምዖን ነገዶች በውርስ የተሰጡትን ልዩ ልዩ ቀበሌዎች አጠቃሎ የያዘ ነበር። የሚዋሰነውም በምሥራቅ ከጨው ባሕርና ከዮርዳኖስ ወንዝ፤ከደቡብ ከጺን ምድረ በዳ፤ከምዕራብ ከታላቁ ባሕር፤ከሰሜን ከሰማርያ ደቡባዊ ወሰን ነበር። ሃይማኖተ ጠንካራ የነበሩ አይሁዶች በዚህ ክፍል መኖራቸው ይታወሳል።


፪፤ <u>ሰማርያ</u> በይሁዳና በገሊላ መካከል ሲሆን ከልዩ ልዩ ነገዶች የተከላለሰ ዘር የነበራቸው ሰዎች መኖሪያ አውራጃ ነበር። ከነዋሪዎቹም ግማሾቹ ከምርኮው በኋላ ወደ አገራቸው የተመለሱት አይሁዶች፤ሌሎቹ ደግሞ እስራኤላውያን አገራቸውን ለቀው በሄዱ ጊዜ በቦታው የተተኩት የውጭ አገር ሕዝቦች ትውልድ እንደ ነበሩ ይነገራል። (፪ ነገሥት ምዕራፍ ፲፯ ተመልከት።)

፫፤ <u>ገሊላ</u> ከቀርሜሎስ ተራራ፣ከታላቁ ባሕርና ከፊንቄ እየተዋሰነ እስከ ሊባኖስ ተራሮች፤ከታላቁ ባሕር እስከ ገሊላ ባሕር የተዘረጋው ሰሜናዊው አውራጃ ነበር። አገሬዎቹም የማይበገሩ ሃይማኖተ ጠንካሮች አይሁዶች ነበሩ። አብዛኛው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት በዚህ አገር ተሰብከአል።

፬፤ <u>ፔሪያ (ዮርዳኖስ ማዶ)</u> በምዕራብ ከዮርዳኖስ ወንዝና ከጨው ባሕር፤በምሥራቅ ከአሥር ከተማና ከዓረብ በረሃ፤በደቡብ ከአርኖን ወንዝ፤በሰሜን እስከ ኢያቢስ ገለዓድ የተዘረጋ አውራጃ ነበር። በዚህ አውራጃ ምንም እንኳ አይሁዶች ቢኖሩ ብዙዎች የአሕዛብ መንደሮች ነበሩ።

፭፤ <u>አሥር ከተማ</u> የግሪኮች መኖሪያ የነበሩትን፤በአይሁዶች የተከበቡትን አሥሩን ልዩ ልዩ ከተሞች የሚያጠቃልል አውራጃ ነበር። እነዚህ በፓሌስቲን የነበሩ ከተሞች በአይሁዶች የተከበቡ ቢሆኑም ሁሉም የአረማውያን መኖሪያ ነበሩ እንጂ የአይሁድ እምነት የነበራቸው ሰዎች አልነበሩባቸውም።

# ፩ኛ ካርታ
# ክፍለ ሐገሮች



# ኢየሩሳሌም

(በገጽ 9 ያለውን ሥዕል ተመልከት ። ይህ ሥዕል ጌታችን በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ የኢየሩሳሌምን ሁኔታ ይገልጣል ።)

ኢየሩሳሌም የፓሌስቲን ዋና ከተማ ነበረች ። የስሙዋም ፍቺ የሰላም መሠረት ማለት ነው ። ይህች ከተማ ከታላቁ በሕር ያላት ርቀት 51 ኪሎሜትር ሲሆን ከጨው በሕር ደግሞ 29 ኪሎሜትር ነው ። ከፍታዋ እስከ 760 ሜትር ይሆናል ።

## ሀ/ ሸለቆዎች

፩ ፤ ቄድሮን የተባለው ሸለቆ አንዳንድ ጊዜም «ኢዮሣፍጥ ሸለቆና» «የንጉሥ ሸለቆ» ይባላል (ኢዩኤል ፫ ፥ ፪ ፤ ፪ ሳሙ. ፲፰ ፥ ፲፰)። አቀማመጡም ከከተማው በስተ ምሥራቅ በደብረ ሞሪያና በደብረ ዘይት መካከል ነው ።

፪ ፤ የሄኖም ልጅ ሸለቆ የከተማውን ዳርቻ በምዕራብና በደቡብ በማዋሰን ከቄድሮን ሸለቆ ጋር ይገናኛል ። በቄድሮን አቅራቢያ ያለው የታችኛው ክፍል ቶፌት ተብሎ ይጠራ ነበር (ኤር. ፯ ፥ ፴፩)። በተጨማሪም አንዳንድ ሰዎች ገሃነም ብለው ሰይመውታል ።

## ለ/ ተራራዎች

፩ ፤ ደብረ ጽዮን በከተማው ክልል ውስጥ ከሚገኙት ተራራዎች በስፋትና በከፍታ ከሁሉ የበለጠ ነው ። አቀማመጡም ከከተማው በስተ ደብብ ምሥራቅ ከቄድሮን ሸለቆ በስተ ምዕራብ በኩል ነው ። ከፍታውም ልክ እስከ ጫፍ ድረስ 770 ሜትር ይሆናል ።

፪ ፤ ደብረ ሞሪያ ቤተ መቅደስ ተሠርቶበት የነበረው ከከተማው በስተ ምሥራቅ በኩል የሚገኘው ተራራ ነው ። ይህ ስፍራ ቤተ መቅደስ ከተሠራበት ወዲህ ብዙ ዘመን ቆይቶ በእስላሞች እጅ ወደቀ ፤ መስጊድም ተሠርቶበት እስከ ዛሬ በእጃቸው ይገኛል ።

፫ ፤ ደብረ ዘይት ከቄድሮን ሸለቆ በስተ ምሥራቅ በኩል ይገኛል ። ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገው ከዚህ ተራራ ላይ ነበር (የሐዋ ፩ ፥ ፲፩—፲፪)። ይህ ተራራ እንደ ጠቀስናቸው እንደ ሁለቱ ተራሮች በከተማው ክልል ውስጥ ሳይሆን ከከተማው ውጭ በስተ ምሥራቅ ይገኛል ። ከፍታውም 800 ሜትር ያህል ነው ።

፬ ፤ የክፉ ጉባኤ ተራራ ከሄኖም ልጅ ሸለቆ በስተ ደቡብ ይገኛል ። ይህም ተራራ የአስቆሮቱ ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ሲሸጥ የቀጋውን ክርክር የወሰኑበት ቦታ ነበር ይባላል ። በተራራው ሸንተረር ላይ አኬልዳማ (የደም መሬት) የተባለው ስፍራ ይገኛል ።

## ሐ/ መንገዶች

(ሁለተኛውን ካርታ ተመልከት)


ወደ ኢየሩሳሌም የሚወስዱ ፬ ዋና ዋና መንገዶች ነበሩ ።

፩ ፤ ሰሜናዊው መንገድ በሰሜን በኩል ወደ ደማስቆ ያመራ ነበር ። በዚህ መንገድ ያዕቆብ ሰማያዊውን መሰላል በሕልም ያየበትና አብርሃምም ተስፋ ወደ ተሰጠው ምድር በገባ ጊዜ ድንኳኑን ተክሎ መሠዊያ የሠራበት ቤቴል ይገኝ ነበር ። (ዘፍጥ. ፳፰ ፥ ፲፩—፳፪ ፤ ፲፪ ፥ ፰)

ጥንታዊት

# ኢየሩሳሌም

የአንድ ሠዓሊ አቀራረብ




፪ ፤ <u>ምሥራቃዊው መንገድ</u> ሰውም ሆነ ወይም ተክል በሌለበት ቦታ ተዘርግቶ ወደ ኢያሪኮ የሚያወርድ ነበር ። በዚህ መንገድ ሲታለፍ የማርያምና የማርታ መኖሪያ ስፍራ ከደብረ ዘይት በስተ ምሥራቅ አግድም የሚገኘው ቢታንያ የተባለው ቀበሌ ይታይ ነበር ።

፫ ፤ <u>ደቡባዊው መንገድ</u> ከኢየሩሳሌም 29 ኪሎሜትር ርቆ ወደሚገኘው ወደ ኬብሮን ይወስድ ነበር ። ማንም እግረ መንገዱን ሲያልፍ የራሔልን መቃብርና ቤተ ልሔምን ሊያይ ይችል ነበር ። ኬብሮን በዓለም ካሉት ጥንታውያን ከተሞች አንዱ ነው ። ከአብርሃም ጊዜ በፊት እንኳ ሕዝብ ኖሮበታል ። እንዲሁም የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች የመቃብር ቦታና የዳዊት የይሁዳ መንግሥት መናገሻ ከተማ ነበር ።

ደቡባዊው መንገድ ኬብሮን ሲደርስ በሁለት አቅጣጫዎች ያመራ ነበር ። አንዱ ተገንጣይ መንገድ ደቡባዊውን አቅጣጫ ይዞ ሲዘልቅ ፤ ሌላው ደግሞ በስተ ደቡብ ምዕራብ ወደ ጋዛ ያወርድ ነበር ። ደቡባዊው ምዕራብ መንገድ ፊልጶስ ኢትዮጵያውን ጃንደረባ የተገናኙበት በምድረ በዳ የሚያልፈው መንገድ ነበር ። (የሐዋ. ፰ ፥ ፳፮—፴፱)

፬ ፤ <u>ምዕራባዊው መንገድ</u> ወደ ኢዮጴ የሚወስድ ሲሆን ከኢየሩሳሌም 7 ኪሎሜትር ራቅ ብሎ በሚገኘው በኤማሁስ መንደር በኩል ያልፍ ነበር ። (ሉቃ. ፳፬ ፥ ፲፫)



፩ኛ ካርታ
የፍልስጥኤም
አውራ መንገዶች
ደማስቆ
ጢሮስ
ቅፍርናሆም
ቤተ ሳይዳ
የገሊላ ባሕር
ገ ሊ ላ
ናዝሬት
ታላቁ ባሕር
የዮርዳኖስ መንገድ
ሰማርያ
ኢዮጴ
ሰ ማ ር ያ
ቤቴ ል
ኢያሪኮ
ኤማሁስ
ኢየሩሳሌም
ቢታንያ
ቤተ ልሔም
ይ ሁ ዳ
ጋዛ
ኬብሮን
የጨው ባሕር
ግብፅ
መለኪያ
0 10 20 30 40 50
በኪሎሜትር

# የክርስቶስ ሕይወት

በዚህ ክፍል ጌታችን የፈጸማቸውን ዋና ዋና ጉዳዮችና በተለይም ስለ ኑበኛቸው በታዎች ትመለከታለህ ። ታሪኩን በምታነብበት ጊዜ የተጠቀሱትን ስሞችና አገሮች በካርታዎቹ ላይ ብትመለከት በጣም ይጠቅምሃል ።

የክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዘጠኝ ክፍሎች ተከፍሎአል ።

## ፩ ፤ የተዘጋጀበት ክፍለ ጊዜ

(ሦስተኛውን ካርታ ተመልከት)

ይህ ክፍለ ጊዜ ከልደቱ እስከ ጥምቀቱ ያሉትን ሠላሳ ዓመታት የሚያጠቃልል ረዥም ጊዜ ሲሆን ስለ ክርስቶስ ሕይወት ያለው መግለጫነት ግን አነስተኛ ነው ።

ሀ / <u>እቤተ መቅደስ መቅረብ</u> ፡— (ከቤተ ልሔም እስከ ኢየሩሳሌም) ዮሴፍና ማርያም ክርስቶስን እቤተ መቅደስ ሲያቀርቡት የ፵ ቀን ሕፃን ነበረ ። በዚህም ጊዜ የእስራኤል መሢህ መሆኑ በስምዖንና በሐና ተረጋገጠ ። (ሉቃ. ፪ ፥ ፳፪—፴፰)።

ለ / <u>ወደ ግብፅ መሰደድ</u> ፡— ሰብአ ሰገል መጥተው ከዩት በኋላ ሕፃኑ ኢየሱስ ወደ ግብፅ ተወሰደ ። ይህም የሆነው ሊገድለው ይፈልግ ከነበረው ከሄሮድስ ለማምለጥ ነበር (ማቴ. ፪ ፥ ፩—፲፰) ። ሕፃኑም ኢየሱስ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በግብፅ ቆይቶአል ።

ሐ / <u>በናዝሬት መቀመጥ</u> ፡— (ከግብፅ ወደ ናዝሬት) ከሄሮድስ ሞት በኋላ ኢየሱስ ከግብፅ ወደ ዮሴፍና ማርያም አገር ወደ ናዝሬት ተወሰደ ፤ የወጣትነቱን ጊዜ እዚሁ አሳልፎአል ። (ማቴ. ፪ ፥ ፲፱—፳፫)


መ / <u>ቤተ መቅደስን መጐብኘት</u> ፡— (ከናዝሬት እስከ ኢየሩሳሌም ደርሶ መልስ) ስለ ኢየሱስ የወጣትነቱን ጊዜ በመከታተል የተጻፈው ይህ ብቻ ነው ። የአሥራ ሁለት ዓመት ወጣት በነበረ ጊዜ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ ። ከዚያም ከማርያምና ከዮሴፍ ጋር ወደ ቤት ሲመለስ ከመንገድ ተነጥሎ ቀረ ፤ ማርያምና ዮሴፍም የሄደበትን ባለማወቅ ተቸግረው ሲፈልጉት ከሦስት ቀናት በኋላ ከመምህራን ጋር በቤተ መቅደስ ሲነጋገር አገኙት ። በኋላም ከዮሴፍና ከማርያም ጋር ወደ ናዝሬት ተመለሰ (ሉቃ. ፪ ፥ ፵—፶፪) ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለ፲፰ ዓመታት ያህል የኢየሱስን ታሪክ በደንብ ተከታትሎ የጻፈ የለም ።

### <u>በዚህ ክፍል የተጠቀሱ ስሞች</u>

፩ ፤ <u>ቤተ ልሔም</u> ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ ምዕራብ ሆኖ 10 ኪሎሜትር ርቀት ያለው ከተማ ነበር ።

፪ ፤ <u>ናዝሬት</u> ከገሊላ አውራጃ በኢይዝራኤል ሸለቆ አጠገብ ይገኝ ነበር ።

፫ ፤ <u>ኢየሩሳሌም</u> (ገጽ ፱ ተመልከት)




፫ኛ ካርታ
የተዘጋጀበት
ክፍለ ጊዜ

## ፪፤ ተግባሩን የጀመረበት ክፍለ ጊዜ

(አራተኛውን ካርታ ተመልከት)

የክርስቶስ ሁለተኛው የዕድሜ ክፍል አሥራ አምስት ወራት ወስዶአል፤ይኸውም ከመጠመቁ ጀምሮ በናዝሬት ሰዎች እስከ ተናቀበት ጊዜ ድረስ ነው። በዚህ ክፍል የአምስት ጉዞዎች ዝርዝር ይገኛል።

ሀ/ መጠመቁ፦— (ከናዝሬት ወደ ቤተ ራባ) ኢየሱስ በዮሐንስ መጥምቁ የተጠመቀውና የአብ ልጅ የመሆኑንም ምስክርነት ከሰማያት የተቀበለው እዚሁ በቤተ ራባ ነበር። (ማቴ. ፫፥፲፫—፲፯)

ለ/ መፈተኑ፦— (ከቤተ ራባ ወደ ምድረ በዳ ደርሶ መልስ) ኢየሱስ ከጥምቀቱ በኋላ ወዲያውኑ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ፤ እዚያም ፵ ቀናት ሙሉ ጾመ፤ የሰይጣንንም ፈተና ድል አደረገ (ማቴ. ፬፥፩—፲፩)። ወደ ቤተ ራባ ተመልሶም የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ስለ መሆኑ የዮሐንስ መጥምቁን ምስክርነት ተቀብሎ የመጀመሪያዎቹን ደቀ መዛሙርት ተገናኛቸው። እነርሱም እንድርያስ፥ጴጥሮስ፥ዮሐንስ፥ፊልጶስና ናትናኤል ነበሩ። (ዮሐ. ፩፥፴፭—፶)

ሐ/ የቃና ዘገሊላ ሠርግ፦— (ከቤተ ራባ እስከ ቃናና ቅፍርናሆም) ኢየሱስ ከቤተ ራባ ወደ ቃና ሄዶ ውኃውን ወይን በማድረግ የመጀመሪያውን ተአምር ፈጸመ። ከዚያም በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ጋር ሆኖ ወደ ቅፍርናሆም ሄደና ለጥቂት ቀናት እዚያ ተቀመጠ።


መ/ ከጥምቀቱ በኋላ የመጀመሪያው ፋሲካ፦— (ከቅፍርናሆም ወደ ኢየሩሳሌም) በኢየሩሳሌም በዚህ በፋሲካው በዓል ኢየሱስ ነጋዴዎቹን ከመቅደስ አስወጣቸው (ዮሐ. ፪፥፲፬—፳፪)። ከኒቆዲሞስም ጋር ስለ ዳግመኛ መወለድ ተነጋገረ። በይሁዳ አገር በቆየ ጊዜ ጥቂቶች ደቀ መዛሙርት ሰበሰበ፤ ግን ዮሐንስ መጥምቁ ገና በስብከት ላይ በመሆኑ የኢየሱስ ስብከት እጅግም በይፋ አልነበረም። (ዮሐ. ፫፥፩—፴፮)

ሠ/ ወደ ገሊላ አውራጃ መመለስ፦— (ከኢየሩሳሌም ወደ ሲከርና ቃና) ኢየሱስ ከይሁዳ አገር ወጥቶ ከበፊቱ ይልቅ በዚህን ጊዜ በይፋ ይሰብክ ጀመር፤ በሰማርያም በኩል ሄዶ ሲከር በተባለው ከተማ በያዕቆብ የውኃ ጉድጓድ አጠገብ ከአንዲት ሳምራዊት ሴት ጋር ተነጋገረ። በቃና ባደረገው ንግግር በቅፍርናሆም ታሞ የነበረውን የአንድ ትልቅ ሰው ልጅ ፈወሰ። (ዮሐ. ፬፥፩—፶፬)

### በዚህ ክፍል የተጠቀሱ ስሞች

፩፤ ቤተ ራባ ከዮርዳኖስ ማዶ ዮሐንስ ያጠምቅበት የነበረው አካባቢ ነበር።

፪፤ «ምድረ በዳ» በጨው ባሕር አጠገብ ያለው፤ ሰው የማይኖርበት ምሥራቃዊው ክፍል ሳይሆን አይቀርም።




፩ኛ ካርታ
ተግባሩን የጀመረበት
ክፍለ ጊዜ

፫፤ <u>ቃና</u> ከናዝሬት በስተ ሰሜን ምዕራብ 13 ኪሎሜትር ያህል ራቅ ያለ ከተማ ነው ። የናትናኤል የትውልድ አገር እዚህ ነበር ። (ዮሐ. ፳፩ ፡ ፪)

፬፤ <u>ቅፍርናሆም</u> ከገሊላ ባሕር በስተ ሰሜን ምዕራብ ጠረፍ የምትገኝ ከተማ ነበረች፤ኢየሱስ በዚህ ስፍራ ለረጅም ጊዜ በመቆየት ብዙ ተአምራት ፈጽሞአል ።

፭፤ <u>ሲካር</u> የያዕቆብ ልጅ ለዮሴፍ ባወረሰው መሬት አጠገብ በሰማርያ አውራጃ የምትገኝ ከተማ ነበረች ። (ዘፍጥ. ፵፰ ፡ ፳፩—፳፪ ፤ ዮሐ. ፬ ፡ ፭)

# ፫፤ የመጀመሪያውን የገሊላ ስብከት ያደረገበት ክፍለ ጊዜ

(አምስተኛውን ካርታ ተመልከት)

ሦስተኛው የክርስቶስ የዕድሜ ክፍል አራት ወራት ያህል ነበር ።

ሀ/ <u>ከቃና እስከ ናዝሬትና ቅፍርናሆም</u>፡— ኢየሱስ ባደገበት ከተማ ለማገልገል ተመኘ፤ነገር ግን የከተማው ነዋሪዎች ከደውት ስለ ነበረ ከእጃቸው ባያመልጥ ኖሮ ይገድሉትም ነበር (ሉቃ. ፬ ፡ ፲፯—፴) ። በመነቀፉ ምክንያት ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም ሄደ፤ ይህንንም ከተማ የሥራው ማዕከላዊ ቦታ አደረገ (ሉቃ. ፬ ፡ ፴፩) ። ዓሣ አጥማጆች የነበሩትን ስምዖንንና እንድርያስን፤ያዕቆብንና ዮሐንስንም እንዲከተሉት የጠራቸው ከዚህ ነበር ። (ሉቃ. ፭ ፡ ፲—፲፩)


ለ/ <u>በምሥራቃዊ ገሊላ መዘዋወር</u>፡— (ከቅፍርናሆም አንሥቶ በምሥራቃዊ ገሊላ በኩል አልፎ መመለስ) ይህ ጉዞ የወሰደው ጥቂት ጊዜ ብቻ ነበር ። ኢየሱስ አንድ ለምጻም ከፈወሰ በኋላ ብዙ ሰዎች ዳግመኛ የበለጠ ተአምር ያዩ ዘንድ በመፈለግ ወደ እርሱ መጡ ። ኢየሱስም ለጥቂት ጊዜ ተለይቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ ። (ሉቃ. ፭ ፡ ፲፪—፲፮)

ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም በተመለሰ ጊዜ በጣራ ያወረዱትን አንድ ሽባ ፈወሰ (ሉቃ. ፭ ፡ ፲፯—፳፮) ። ቀራጭ የነበረውንም ማቴዎስን ደቀ መዝሙሩ ይሆን ዘንድ ጠራው ። (ሉቃ. ፭ ፡ ፳፯—፳፰)

ሐ/ <u>ከጥምቀቱ በኋላ ዳግመኛው የፋሲካ በዓል</u>፡— (ከቅፍርናሆም ወደ ኢየሩሳሌም ደርሶ መልስ) በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ማስተማር ከጀመረ ሁለተኛ ዓመቱ ነበር ። እርሱም ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ አንድ ድውይ በቤተ ሳይዳ መጠመቂያ ዳርቻ አዳነ (ዮሐ. ፭ ፡ ፩—፵፯) ። ከዚያም ሲመለስ የሰንበት ጌታ ኢየሱስ ራሱ መሆኑን አስታወቀ (ሉቃ. ፮ ፡ ፩—፭) ። በኋላም በአንድ የሰንበት ቀን እጁ የሰለለችውን ሰው በምኩራብ ውስጥ አዳነው ። (ሉቃ. ፮ ፡ ፮—፲፩)

መ/ <u>የተራራው ስብከት</u>፡— (ከቅፍርናሆም ወደ ተራራ መሄድ) ፈሪሳውያን ብዙ መቃወም ስላበዙበት ኢየሱስ ቅፍርናሆምን ለቅቆ ሕዝቡን በባሕር ጠረፍ ሊያስተምር ሄደ (ማር. ፫ ፡ ፯—፲፪) ። ከዚያም ወደ ተራራ ወጣና ሌሊቱን ሙሉ ሲጸልይ አደረ፤ቀጥሎም ደቀ መዛሙርቱ መሆን የሚገባቸውን መረጠ ። ያን ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱና ለተሰበሰበው ሕዝብ ስብከቱን በዚያው ተራራ ላይ አሰማ ። (ማቴዎስ ከምዕራፍ ፭ እስከ ፯)

በዚህ ጉዞ የተጠቀሱትን ልዩ ልዩ ቦታዎች ቀደም አድርገን ገልጸናል ።


፩ኛ ካርታ
የመጀመሪያውን የገሊላ
ስብከት ያደረገበት
ክፍለ ጊዜ
ቅፍርናሆም
ቃና
ገ ሊ ላ
የገሊላ ባሕር
ናዝሬት
ምድረ በዳ
ታላቁ ባሕር
ሰ ማ ር ያ
የዮርዳኖስ ወንዝ
ኢየሩሳሌም
ይ ሁ ዳ
የጨው ባሕር
መለኪያ
0 10 20 30 40 50
በኪሎሜትር

# ፬ ፤ ሁለተኛውን የገሊላ ስብከት ያደረገበት ክፍለ ጊዜ

(ስድስተኛውን ካርታ ተመልከት)

በዚህ ጊዜ የኢየሱስ ክፍለ ዕድሜ ለአሥር ወራት ያህል ነበር ። በዚህ ክፍለ ጊዜ አብዛኛዎቹ ባለሥልጣኖች ትምህርቱን ቢነቅፉም ተራው ሕዝብ ተቀብሎታል ።

ሀ / <u>ወደ ደቡባዊ ገሊላ መጓዝ</u> ፡— (ከቅፍርናሆም ወደ ናይን ደርሶ መልስ) ክርስቶስ የአንድ የመቶ አለቃ ባርያ ባዳነ ማግስት (ሉቃ· ፯ ፥ ፩—፲) ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ወደ ደቡብ ወደ ናይን ሄዶ የአንዲት ባልቴት ወንድ ልጅ ከሞት አስነሣ። (ሉቃ· ፯ ፥ ፲፩—፲፯)

በዚህ ጉዞ ላይ ሳለ ኃጢአተኛ የነበረች አንዲት ሴት በአጠገቡ ቆማ እግሩ እስኪ ርስ ድረስ ታለቅስ ነበር (ሉቃ· ፯ ፥ ፴፯—፶) ። ከናይን በተመለሰ ጊዜ ኢየሱስ ጋኔን የሚ ያወጣው በአጋንንት አለቃ ኃይል ነው በማለት ፈሪሳውያን ይናገሩ ነበር ። (ሉቃ· ፲፩ ፥ ፲፬—፳፯)

ለ / <u>ወደ ጌርጌሴኖን አገር መጓዝ</u> ፡— (ከቅፍርናሆም ወደ ጌርጌሴኖን ደርሶ መልስ) የጠላቶቹ መቃወም መበርታት ከተማውን እንዲለቅና በምሳሌም እንዲያስተምር አደረገው (ማቴ· ፲፫ ፥ ፩—፶፫) ። ወደ ጌርጌሴኖን አገር በባሕር ጉዞ ላይ ሳለ ማዕበሉን በመገሠፅ ጸጥ አሰኘው (ማር· ፬ ፥ ፴፭—፵፩) ። በባሕሩ ምሥራቃዊ ጠረፍ በጌርጌሴኖን አገር ርኩስ መንፈስ ያላቸውን ሁለት ሰዎች ከፈወሰ በኋላ ርኩሳን መናፍስትም በእርያዎች እን ዲገቡ ፈቀደ ። ስለዚህም አገሬው ከዚያ ለቅቆ እንዲሄድ ጠየቀ ። እርሱም በሕሩን አቋ ርጦ ወደ ቅፍርናሆም መጣና የኢያኢሮስን ሴት ልጅ ከሞት አስነሣት ። (ሉቃ· ፰ ፥ ፵፩—፶፮)

ሐ / <u>ወደ ቤተ ሳይዳ ተለይቶ መሄድ</u> ፡— (ከቅፍርናሆም ወደ ቤተ ሳይዳ ደርሶ መልስ) ኢየሱስ በቤተ ሳይዳ ከሕዝቡ ተለይቶ ለጥቂት ጊዜ ቆየ (ማር· ፮ ፥ ፴፩—፴፪) ። የተከተሉትንም አምስት ሺህ ሕዝብ ካስተማራቸው በኋላ በ፭ እንጀራና በ፪ ዓሣ አጠገባ ቸው (ማር· ፮ ፥ ፴፪—፵፬) ። ከዚያም ትንሽ ቆይቶ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ማዶ ወደ ቅፍ ርናሆም አስቀድሞ ላከና በመንፈቀ ሌሊት በውኃ ላይ እየተራመደ ወደ እነርሱ ሄደ (ማር· ፮ ፥ ፵፭—፶፪) ። በማግሥቱም በጌንሴሬጥ ጠረፍ በቅፍርናሆም አቅራቢያ ጀልባቸውን አሳረፉ ። እዚህ ክርስቶስ ብዙ ተአምራት አደረገ (ማር· ፮ ፥ ፶፫—፶፯) ። ወደ ቅፍርናሆ ምም ተመልሶ በምኩራብ ስለ ሕይወት እንጀራ ብዙ በመነጋገር የገሊላ ስብከቱን አበቃ ። (ዮሐ· ፮ ፥ ፳፭—፶፱)


## <u>በዚህ ክፍል የተጠቀሱ ስሞች</u>

፩ ፤ <u>ናይን</u> ከናዝሬት በስተ ደቡብ ምሥራቅ 10 ኪሎሜትር ራቅ ያለች ከተማ ነበረች ።

፪ ፤ <u>የጌርጌሴኖን አገር</u> ከገሊላ ባሕር በስተ ምሥራቅ ይገኝ ነበር ።

፫ ፤ <u>ቤተ ሳይዳ</u> ከገሊላ ባሕር በስተ ሰሜን ምሥራቅ የሚገኝ ከተማ ነበር ።

፬ ፤ <u>ጌንሴሬጥ</u> በቅፍርናሆም አቅራቢያ የሚገኝ አገር ነበር ።


፭ኛ ካርታ
ሁለተኛውን የገሊላ ስብከት
ያደረገበት ክፍለ ጊዜ
ቅፍርናሆም
ቤተ ሳይዳ
ጌንሴሬጥ
የጌርጌሴኖን አገር
ቃና
የገሊላ ባሕር
ገ ሊ ላ
ናዝሬት
የዮርዳኖስ ወንዝ
ናይን
መለኪያ
0 5 10 15
በኪሎሜትር

## ፳፤ በአሕዛብ ወገኖች ዘንድ

(ሰበተኛውን ካርታ ተመልከት)

የኢየሱስ አምስተኛ ክፍለ ዕድሜ ብዛት ስድስት ወር ነበር ።

ሀ/ ወደ ፊንቄ መጓዝ ፡— (ከቅፍርናሆም እስከ ጢሮስና ሲዶና ዳርቻ ድረስ) ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎቹ ኢየሱስ ስለ ሕይወት እንጀራ ያደረገውን ንግግር ከዳመጡ በኋላ ሊከተሉት አልፈቀዱም (ዮሐ. ፮ ፡ ፷—፷፮) ። እርሱም ወደ ጢሮስና ሲዶና ዳርቻ (ወደ ፊንቄ አገር) ሄዶ የሲሮፊኒቃዊት ወገን የነበረችውን አንዲት ሴት ልጅ ርኩስ መንፈስ አስወጣላት ። (ማር. ፯ ፡ ፳፬—፴)

ለ/ ወደ አሥር ከተማ መጓዝ ፡— (ከጢሮስና ከሲዶና ዳርቻ ወደ አሥር ከተማ) ኢየሱስ ከፊንቄ ወደ አሥር ከተማ ሄዶ (ማር. ፯ ፡ ፴፩) አንድ ደንቆሮ ሰው በመፈወስና ፬ ሺ ሰዎች በመመገብ ሁለት ተአምራት ፈጸመ ። (ማር. ፯ ፡ ፴፪—፴፯ ፤ ፰ ፡ ፩—፱)

ሐ/ ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር መጓዝ ፡— (ከአሥር ከተማ ወደ ዳልማኑታ ፡ ቤተ ሳይዳና ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር) ኢየሱስ ሐይቁን በጀልባ አቋርጦ ወደ ዳልማኑታ ተጓዘ ። እዚያም ፈሪሳውያን ምልክት እንዲያሳያቸው ፈለጉ (ማር. ፰ ፡ ፲—፲፪) ፤ ቀጥሎም ወደ ሰሜን አቅጣጫ ወደ ቤተ ሳይዳ በጀልባ ተጉዞ አንድ ዓይነ ስውር ፈወሰ (ማር. ፰ ፡ ፳፪—፳፮) ። እርሱም በዮርዳኖስ ሸቅብ አልፎ በአርሞንዔም ተራራ ሥር ወደ ነበረው ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ ሲደርስ አያሌ ቀናት ተቀመጠ ። በዚህ ቦታ የተፈጸሙ ሦስት ነገሮች አሉ ። እነዚሁም የሚከተሉት ናቸው ፡—

፩፤ ኢየሱስ «ከእግዚአብሔር የተቀባ» ለመሆኑ የጴጥሮስ ምስክርነት ።

፪፤ የክርስቶስ ወደ ብርሃናዊ መልክ መለወጥ ።

፫፤ ርኩስ መንፈስ ያደረበትን ልጅ መፈወስ ። (ሉቃ. ፱ ፡ ፲፰—፵፫ ተመልከት ።)


መ/ የመጨረሻው የቅፍርናሆም ጉብኝት ፡— ከፊልጶስ ቂሣርያ አገር ተነሥቶ ክርስቶስ ወደ ቅፍርናሆም ተመልሶ ሄደ ። (ማር. ፱ ፡ ፴—፺)

### ከዚህ በፊት ያልተጠቀሱ ስሞች

፩፤ ጢሮስና ሲዶና በታላቁ ባሕር ጠረፍ ላይ የነበሩ የፊንቃውያን ከተሞች ነበሩ ።

፪፤ ዳልማኑታ በገሊላ ባሕር ምዕራባዊ ዳርቻ ላይ የምትገኝ አንዲት ከተማ ነበረች ።

፫፤ ፊልጶስ ቂሣርያ በአርሞንዔም ተራራ ሥር የምትገኝ ከተማ ነበረች ።



፲፫ኛ ካርታ
በአሕዛብ
ወገኖች ዘንድ
ሲዶና
የአርሞንዔም ተራራ
ጢሮስ
ፊንቄ
የዮርዳኖስ ወንዝ
ፊልጶስ ቂሣርያ
ታላቁ ባሕር
ቅፍርናሆም
ቤተ ሳይዳ
ዳልማኑታ
የገሊላ ባሕር
ገ ሊ ላ
አሥር ከተማ
መለኪያ
0 10 20 30 40 50
በኪሎሜትር

# ፯ ፤ በይሁዳ የሰበከበት ክፍለ ጊዜ

(ስምንተኛውን ካርታ ተመልከት)


ስድስተኛው የክርስቶስ ክፍለ ዕድሜ የሦስት ወር ጊዜ ነበር ።

ሀ / ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም መጓዝ ፡— ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ቅፍርናሆምን ትቶ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ ። በሰማርያ ጠረፍ ሲያስተምር አገሬው አልተቀበለውም (ሉቃ. ፱ ፥ ፶፩—፶፮) ። እዚህም በነበረበት ዘመን አሥር ለምጻሞች ሲፈውስ ከእነዚህ አንዱ ብቻ ሊያመሰግነው ተመለሰ (ሉቃ. ፲፯ ፥ ፲፩—፲፱) ። ለጊዜው ማረፊያውን በቢታንያ በማርታ ፥ በማርያምና በአልዓዛር ቤት አደረገ (ሉቃ. ፲ ፥ ፴፰—፵፪) ። ኢየሩሳሌም በነበረ ጊዜ በዮሐንስ ወንጌል ከምዕራፍ ፯ እስከ ፲ ያለውን ትምህርት አስተማረ ። ከመወለዱም ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው ፈወሰ ። (ዮሐ. ፱ ፥ ፩—፵፩)

ለ / ከኢየሩሳሌም ወደ ቤተ ራባ መጓዝ ፡— ክርስቶስ ትምህርቱን የሚቃወሙ በብዛት ስለ ተነሡ ከተማውን ትቶ ወደ ተጠመቀበት ወደ ቤተ ራባ ሄደ ። (ዮሐ. ፲ ፥ ፴፱—፵፪)

ከዚህ በፊት ያልተጠቀሰ ስም

ቢታንያ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ደብረ ዘይት ከሚባለው ተራራ ላይ የምትገኝ ትንሽ መንደር ነበረች ።



፫ኛ ካርታ
በይሁዳ የሰበከበት
ክፍለ ጊዜ
ቅፍርናሆም
የገሊላ ባሕር
ገ ሊ ላ
ታላቁ ባሕር
ሰ ማ ር ያ
የዮርዳኖስ ወንዝ
ቤተ ራባ
ኢየሩሳሌም
ቢታንያ
ይ ሁ ዳ
የጨው ባሕር
መለኪያ
0 10 20 30 40 50
በኪሎሜትር

# ፯፤ የዮርዳኖስ ማዶ (ፌርያ) ስብከት ክፍለ ጊዜ

(ዘመነኛውን ከርታ ተመልከት)

ይህ ሰባተኛው የክርስቶስ ክፍለ ዕድሜ የአራት ወራት ጊዜ ነበር ።

ሀ/ ከቤተ ራባ ወደ ቢታንያ ፡— ኢየሱስ ከቤተ ራባ ውጭ ሄደው እንዲሰብኩ ሰባ ሰዎች ላከ ። እዚያው እንደ ነበረ በቢታንያ የሚገኘው ወዳጁ አልዓዛር ስለ ሞተ ሄዶ ከሙታን አስነሣው ። (ሉቃ. ፲ ፥ ፩—፲፯፤ ዮሐ. ፲፩ ፥ ፩—፶፫)

ለ/ ወደ ዮርዳኖስ ማዶ (ፌርያ) መሄድ ፡— ኢየሱስ በዮርዳኖስ ማዶ ያከናወነው ሁሉ የሚከተሉትን ይጠቀልላል ።

፩፤ አንዲት በሕመም የጉበጠች ሴትና አንድ የሆድ በሽታ ያደረበት ሰው ማዳን ። (ሉቃ. ፲፫ ፥ ፲—፲፯፤ ፲፬ ፥ ፩—፯)

፪፤ ታላላቅ ትምህርተ ምሳሌዎች ማስተማር ። (ሉቃ. ከምዕራፍ ፲፬ እስከ ፲፯)

፫፤ ሕፃናትን መባረክ ። (ሉቃ. ፲፰ ፥ ፲፭—፲፯)

፬፤ ለአንድ ባለጠጋ ጥያቄ መልስ መስጠት ። (ሉቃ. ፲፰ ፥ ፲፰—፴)

ሐ/ ከኢያሪኮ ወደ ቢታንያ ፡— ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ በኢያሪኮ በኩል ነበር ። በዚህ ጉዞ የሚከተሉትን እንመለከታለን ።


፩፤ በኢያሪኮ የዕውሩ በርጤሜዎስ መፈወስ ። (ሉቃ. ፲፰ ፥ ፴፭—፵፫)

፪፤ የቀራጮች አለቃ የነበረውን የዘኬዎስን ቤት መጐብኘት ። (ሉቃ. ፲፱ ፥ ፩—፲)

፫፤ በዚህ ጉዞ መጨረሻ ላይ የቢታንያዪቱ ማርያም ኢየሱስን በሽቱ መቀባት ። (ዮሐ. ፲፪ ፥ ፩—፰)

## ከዚህ በፊት ያልተጠቀሰ ቦታ

ኢያሪኮ፤ ኢየሱስ በዚህ ዓለም በኖረበት ጊዜ በዮርዳኖስ ሸለቆ ከሚገኙት ከተሞች ሁሉ ይበልጥ የነበረው ፤ ከኢየሩሳሌም 27 ኪሎሜትር ወደ ምዕራብ የሚገኘው ከተማ ነበር ።


፱ኛ ካርታ
የዮርዳኖስ ማዶ
ስብከት ክፍለ ጊዜ
የዮርዳኖስ ወንዝ
የዮርዳኖስ
ማዶ
ኢያሪኮ
ቤተ ራባ
ኢየሩሳሌም
ቢታንያ
ይ ሁ ዳ
የጨው ባሕር
መለኪያ
0 5 10 15
በኪሎሜትር
አርኖን ወንዝ

# ፰፤ የሥቃይ ክፍለ ጊዜ

ይህም ስምንተኛው ክፍለ ጊዜ ብዛቱ አንድ ሳምንት ብቻ ነው ። ይኸውም በቢታንያ ማርያም ሽቱ ከቀባችው ጀምሮ በመስቀል ላይ እስከሞተበት ድረስ ያለው ጊዜ ነው ። በዚህ ክፍለ ጊዜ የሆነው ሁሉ በኢየሩሳሌም ከተማና በአካባቢዋ ነበር ። በዚያን ጊዜ ኢየሩሳሌም የነበራትን ሁናቴ የሚያሳይ ሥዕል በገጽ ፱ ይገኛል ።

ሀ/ <u>ከቢታንያ እስከ ቤተ መቅደስ ደርሶ መልስ</u>፡— ከቢታንያ እስከ ቤተ መቅደስ ደርሶ የተመለሰው ሦስት ጊዜ ነበር ።

፩፤ ከስቅለቱ በፊት በነበረው እሑድ ኢየሱስ «ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ» እያሉ በተከተሉት ሰዎች ታጅቦ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ (ማቴ. ፳፩ ፥ ፩—፲፩) ። እቤተ መቅደስም ገብቶ በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ፥ ገንዘብ ለዋጮችንም አስወጣ ። ቤተ መቅደስን ሲያጸዳ ይህ በሕይወቱ ሁለተኛ ጊዜው ነበር ። (ማቴ. ፳፩ ፥ ፲፪—፲፯)

፪፤ በማግሥቱ ሰኞ ዕለት ወደ ቤተ መቅደስ ተመልሶ የካህናት አለቆችንና የሕዝቡን ሽማግሎች ሲያስተምር ዋለ ። (ማቴ. ፳፩ ፥ ፲፰—፳፪ ፥ ፲፬)

፫፤ ቀጥሎም ማክሰኞ ዕለት ኢየሱስ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ ተመልሶ ከጠላቶቹ ጋር ተከራከረ ። በኋላም ወደ ደብረ ዘይት ሄደ ። ለደቀ መዛሙርቱ ስለ መጨረሻዎቹ ነገሮች አስተማረ ። (ማቴ. ፳፪ ፥ ፲፭—፳፭ ፥ ፵፮)

ስለ ረቡዕ ዕለት የተጻፈ የለም ።

ለ/ <u>ከቢታንያ የመጨረሻው እራት እስከተበላበት ሰፍራ ድረስ</u>፡— የመጨረሻው እራት የተበላው ከዚሁ ከስቅለቱ በፊት በነበረው ሳምንት ሐሙስ ማታ ነበር ። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለመጨረሻ ጊዜ አብሮ እራት ከመብላቱም በላይ ለመጨረሻም ጊዜ ከመሞቱ በፊት አስተማራቸው ። (ዮሐንስ ከምዕራፍ ፲፫ እስከ ፲፯)

ሐ/ <u>ከመጨረሻው እራት በኋላ ወደ ጌቴሴማኒ መሄድ</u>፡— ሐሙስ ማታ ፤ የመጨረሻው እራት እንዳበቃ ፤ ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ወደ ጌቴሴማኒ አትክልት ቦታ መጣና ከደቀ መዛሙርቱ ለየት ብሎ ጸለየ ። ከዚያም በኋላ ከካህናት አለቆችና ከሕዝቡ ሽማግሎች ተልከው በአስቆሮቱ ይሁዳ እየተመሩ የመጡት ሰዎች ኢየሱስን ይዘው አሰሩት ። (ማቴ. ፳፮ ፥ ፴፮—፶፮)

መ/ ከጌቴሴማኒ <u>ወደ ቀያፋ ቤት</u>፡— ኢየሱስ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ታስሮ እየተጐተተ መጀመሪያ ወደ ሐና ቤት (ዮሐ. ፲፰ ፥ ፲፫—፲፬) ፤ ከዚያም ወደ ቀያፋ ቤት ተወሰደና በአይሁድ ሸንጎ ፊት ለፍርድ ቀረበ ፤ እነርሱም ፈረዱበት ፤ አሽከሮቻቸውም ቀለዱበት ። (ዮሐ. ፲፰ ፥ ፲፱—፳፰)

ሠ/ <u>ከቀያፋ ወደ ጲላጦስ</u>፡— ጲላጦስ ኢየሱስን መርምሮ ጥፋት እንደሌለበት ተረዳና ሊለቀው ሞከረ ። (ዮሐ. ፲፰ ፥ ፳፰—፴፰)

ረ/ <u>ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ ተወስዶ መመለስ</u>፡— ሉቃ. ፳፫ ፥ ፰—፲፪ ተመልከት ።

ሰ/ ከጲላጦስ ዘንድ ወደ ጎልጎታ መወሰድ፦ ጎልጎታ እንደ ደረሰ ተሰቀለ፤ነፍሱንም «ተፈጸመ» አለና አሳልፎ ሰጠ። (ዮሐ. ፲፱፥፩—፴፺)

## ፱፤ የትንሣኤው ክፍለ ጊዜ

በትንሣኤውና በእርገቱ መካከል ባሉት ፵ ቀናት ውስጥ ኢየሱስ ብዙ ጊዜያት ታይቶአል። በትንሣኤው ዕለት እንኳ የታየው አምስት ጊዜያት ነበር። በትንሣኤው ዕለትና ከሌሎቹም ሁኔታዎች በንዳንዶቹ የታየው እንደሚከተለው ነበር፦

ሀ/ ለማርያም መግደላዊት በኢየሩሳሌም ታየ። (ዮሐ. ፳፥፩—፲፰)

ለ/ በኢየሩሳሌም ለሴቶች በመንገድ ላይ ታያቸው። (ማቴ. ፳፰፥፩—፲)

ሐ/ በኤማሁስ ለሁለቱ ደቀ መዛሙርት ታየ። (ሉቃ. ፳፬፥፲፫—፴፩)

መ/ በኢየሩሳሌም ለስምዖን ጴጥሮስ ታየ። (ሉቃ. ፳፬፥፴፫—፴፭)

ሠ/ በኢየሩሳሌም ለአሥሩ ደቀ መዛሙርት ታየ፤ቶማስ ግን አልነበረም። (ዮሐ. ፳፥፲፱—፳፭)

ረ/ በኢየሩሳሌም ከአንድ ሳምንት በኋላ ኢየሱስ እንደገና ለደቀ መዛሙርቱ ታየ። በዚህ ጊዜ ቶማስ እዚያ አብሮ ተገኝቶ ስለ ነበረ፤ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ እንደ ታያቸው ቢነግሩት ባለማመኑ ኢየሱስ ወቀሰው። (ዮሐ. ፳፥፳፮—፳፱ )

ሰ/ በገሊላ ባሕር አጠገብ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ልዩ አደራ ሰጠው። (ዮሐ. ፳፩፥፩—፳፪)

ሸ/ ኢየሱስ በገሊላ በአንድ ተራራ ላይ ለአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ተገልጦ ወደ ዓለም ሄደው እንዲያስተምሩ አዘዛቸው። (ማቴ. ፳፰፥፲፮—፳)

ቀ/ ኢየሱስ አንድ ጊዜ ከ500 ለሚበልጡ ሰዎች ተገለጠ። (፩ ቆሮ. ፲፭፥፮)

በ/ ለወንድሙ ለያዕቆብ ታየ (፩ ቆሮ. ፲፭፥፯)። ስፍራው ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተለይቶ አልተጠቀሰም።

ተ/ ትንሣኤው ባለፈ በ፵ኛው ቀን በቢታንያ አጠገብ ለአሥራ አንዱ ሐዋርያት ታይቶ የመጨረሻ ቃሉን አሰማቸውና ወደ ሰማይ አረገ። (የሐዋ. ፩፥፱—፲፪)

# የስሞች ማውጫ ሠንጠረዥ


| ስም | የካርታ ቍጥር |
|---|---|
| **ሰ** | |
| ሰማርያ | 1, 2, 3, 4, 5, 8 |
| ሰማርያ (ከተማ) | 2 |
| ሲካር | 4 |
| ሲዶና | 7 |
| **ቀ** | |
| ቃና | 4, 5, 6 |
| ቅፍርናሆም | 2, 4, 5, 6, 7, 8 |
| **በ** | |
| ቢታንያ | 2, 8, 9 |
| ቤተ ልሔም | 2, 3 |
| ቤተ መቅደስ | ፨ |
| ቤተ ራባ | 4, 8, 9 |
| ቤተ ሳይዳ | 2, 6, 7 |
| ቤቴል | 2 |
| **ተ** | |
| ታላቁ ባሕር | 1, 2, 3, 4, 5, 7, 8 |
| **ነ** | |
| ናዝሬት | 2, 3, 4, 5, 6 |
| ናይን | 6 |
| **አ** | |
| አሥር ከተማ | 1, 7 |
| ኢየሩሳሌም | 1, 2, 3, 4, 5, 8, 9 ፨ |
| ኢያቢስ ገለዓድ | 1 |
| ኢያሪኮ | 2, 9 |
| ኢዮጴ | 2 |
| ኤማሁስ | 2 |
| **ከ** | |
| ኬብሮን | 2 |

| ስም | የካርታ ቍጥር |
|---|---|
| **የ** | |
| የሄሮድስ ግቢ | ፨ |
| የሄኖም ልጅ ሸለቆ | ፨ |
| የሊባኖስ ተራራዎች | 1 |
| የቀርሜሎስ ተራራ | 1 |
| የቄድሮን ሸለቆ | ፨ |
| የአርሞንዔም ተራራ | 7 |
| የአርኖን ወንዝ | 1, 9 |
| የክፉ ጉባዔ ተራራ | ፨ |
| የዓረብ በረሃ | 1 |
| የዮርዳኖስ ማዶ (ፌርያ) | 1, 9 |
| የዮርዳኖስ ወንዝ | 1, 2, 3, 4, 5, 6, 7, 8, 9 |
| የገሊላ ባሕር | 1, 2, 3, 4, 5, 6, 7, 8 |
| የጌርጌሴኖን አገር | 6 |
| የጨው ባሕር | 1, 2, 3, 4, 5, 8, 9 |
| የጺን ምድረ በዳ | 1 |
| ይሁዳ | 1, 2, 3, 4, 5, 8, 9 |
| **ደ** | |
| ደማስቆ | 2 |
| ደብረ ሞሪያ | ፨ |
| ደብረ ዘይት | ፨ |
| ደብረ ጽዮን | ፨ |
| ዳልማኑታ | 7 |
| **ገ** | |
| ገሊላ | 1, 2, 3, 4, 5, 6, 7, 8 |
| ጋዛ | 2 |
| ጌቴሴማኒ | ፨ |
| ጌንሴሬጥ | 6 |
| ግብፅ | 1, 2, 3 |
| **ጠ** | |
| ጢሮስ | 2, 7 |
| **ፈ** | |
| ፊልጶስ ቂሣርያ | 7 |
| ፌንቄ | 1, 7 |
| ፌርያ (የዮርዳኖስ ማዶ) | 1, 9 |


፨ በገጽ 9 የሚገኘውን ሥዕል ተመልከት።